## ርእሰ አንቀጽ ።

# አብዮት ልጆቿን ስትበላ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለነፃነቷና ለክብሯ ባደረገችው የረዥም ጊዜ ተጋድሎ ብዙ ልጆቿን ሰውታለች ። በየካቲትም ሆነ ከየካቲት በኋላ ዛሬ የተጐናጸፍናቸው ድሎች ተዘርተው የለመለሙት ታጋይ ኢትዮጵያውያን አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ ይቺን የነፃነት ተክል ለማለምለም ደማቸውን በመለገሳቸው ነው ። በተለይ የየካቲት አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከፈነዳበት ወቅት አንስቶ ታጋይ ገበሬዎች ፣ መለዮ ለባሾች ፣ ወዝአደሮች ፣ ዘማች ተማሪዎች ፣ አዝማች መምህራንና ምሁራን በየጊዜውና በየቦታው በነፃነቱ ትግል በግንባር ቀደምትነት ለመጋፈጥ ሕይወታቸውን ለውዲ አገራቸው ሰውተዋል ። ወደፊትም ቢሆን ለአብዮታችን መግፋት ፣ ለሀገራችን ነፃነት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደማቸውን ለማፍሰስ ሌሎች ታጋዮች ከትግሉ እንደሚፈልቁ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው ። የሕዝቦች የነፃነት ታሪክ የሚጻፈው በታጋዮች ደም ነው የሚባለው ለዚህ ነው ። አብዮት ልጆቿን ትበላለች የሚባለውም ለዚህ ነው ።

በዚህ በያዝነው ሰሞን በነፃነቱ ትግል ጐዳና ላይ ለአብዮታችን እጅግ ይጠቅማሉ የምንላቸው ጓዶቻችን በአድኃሪ ኃይሎች አደጋ እየተጣለባቸው ሕይወታቸውን ሰውተዋል ። እሁድ መስከረም አሥራ ስድስት ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. በጥናት ክበባቸው ውስጥ ተሰብስበው የማርክሲዝም ፍልስፍና በሚያጠኑ ሰባት ወጣት አብዮታውያን ላይ አድኃሪዎች ተኩስ ከፍተው በክሬ አብዱልመጅድ ፣ ክንፈ አስፋውና ገብረ እግዚአብሔር ተስፋዬ የተባሉ ወጣት ጓዶቻችንን ገድለዋል ። ዓርብ መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. ጓድ ፍቅሬ መርዕድ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ ቤት የጊዜያዊ ጉዳዮች ኮሚቴ ሊቀ መንበር በመኪና ውስጥ እንዳለ እንደዚሁ በአድኃሪዎች ተገድሏል ። በዚሁ ዕለት ጓድ ጌታቸው እንግዳ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ ቤት የአዲስ አበባና አካባቢው ባልደረባ የነበረ ጓዳችን ከቤቱ ደጃፍ ተገድሏል ። በየመንደሩና በየቀበሌው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በወጣት አብዮታውያን ላይ ከፍተኛ የውንብድና ተግባር እየተፈጸመባቸው መሆኑንና በጠቅላላው አድኃሪ ኃይሎች አዲስ አበባ ውስጥ መሽገው ይቺን ከተማ የሽብር ከተማ ሊያደርጓት በመፍጨርጨር ላይ መሆናቸው በየጊዜው ከሚሰሙት ዜናዎች ለመረዳት ይቻላል ።

በማንኛውም አብዮት ጊዜ አድኃሪ ኃይሎች ጨርሰው ተጋልጠው በፖለቲካው ትግል በኩል መፈናፈኛ ሲያጡ የባርነት ቀንበራቸውን ዘመን በዚህ ያሳጠሩ እየመሰላቸው ተሽቀዳድመው መሣሪያ ያነሣሉ ። እርግጥ ሁሉም አድኃሪ ይህንን የመሣሪያ ትግል በአንድነት አይጀምረውም ። በመደብ አቋሙ ምንም ዓይነት የተራማጅነት ካባ ደርቦ ለማወናበድ የማይችለው የለየለት አድኃሪ የትጥቅ ትግሉን ቀደም ብሎ ይጀምራል ። ነገር ግን የፖለቲካው ትግል እየተፋፋመ ሲሄድና ተራማጅ ካባ ያጠለቁ አድኃሪዎች ፣ ወይም በአብዮታዊው ትግል ታልፈው እንዲሄዱ ያልተነቃባቸው የትላንት ተራማጆች በአድኃሪ ገጽታቸው ሙሉ በሙሉ ይጋለጣሉ ። ያን ጊዜ በፖለቲካው ትግል ጨርሶ ተስፋ ይቆርጡና ቀደም ሲሉ ተጋልጠው ቀደም ብለው መሣሪያቸውን አንስተው በሕዝቡ ላይ ያመጹትን አድኃሪዎች ይደባልቋቸዋል ።

በሀገራችን የቀኙ ክንፍ ከበርቴ የተጓዘበት የክስረትና የክህደት ጐዳና ይህንን የመሰለ ነው። የአብዮቱ መግፋት ጨርሶ አጋልጦ ርቃኑን እስካላስቀረው ድረስ ተራማጅ መስሎ ለማወናበድ ሞክሮ ነበር ። ነገር ግን የርእዮተ ዓለሙ ትግል ከሚችለው በላይ ሆነበት ። በሀገራችን የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ርእዮተ ዓለም መስፋፋት የቀኙን ክንፍ ንዑስ ከበርቴ የከሰረ ፖለቲካ ማጋለጫ ብርሃን ሆነ ። ይህ አድኃሪ ክንፍ ከዚህ ከፍተኛ ኪሳራ ላይ ከመድረሱ በፊት የሶሻሊዝም ፍልስፍና እንዳይስፋፋ መጻሕፍት ቤቶችን ማስደብደብና ማስዘረፍ ፣ ከአድኃሪና አደናቋሪ ጋዜጣው በስተቀር ሌላ እንዳይነበብ ታጋይና ተመራማሪ ወጣቶችን በጠራቢ ቡድን ማስደብደብ ሥራዬ ብሎ የያዘው ዘይቤ እንደነበረ እናውቃለን ። ግን ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ መፍጨርጨር የኢትዮጵያ ወጣቶች ለማወቅና ለመመራመር ያላቸውን ከፍተኛ ጉጉት ሊያፍነው እንደማይቻል ግልጽ ነበር ። ስለሆነም በማርክሲዝም መስፋፋትና በርእዮተ ዓለሙ ትግል መፋፋም የተጋለጠውና የተደናገጠው የአናርኪስቶች ቡድን አሁንም መፍጨርጨሩን ቀጠለ ። በሀገራችን ማሰብ የጀመሩትን የማርክሲስት የጥናት ክበቦች ለማፈን በቀጥታ መትረየስ እየያዙ ክበቦችን መረሸን ጀመረ ። የርእዮተ ዓለሙን ትግል ለማፈን በዚህ በኩል ተሰማርተው የኢሕአፓን የከሰረ አድኃሪ መስመር ለማጋለጥ በሚታገሉ ሐቀኛ ተራማጆች ላይ የግድያ ሴራ ጠነሰሰ ።

የነጓድ ፍቅሬ መርዕድ መገደል ከዚህ ከአናርኪስቶች የፖለቲካ ክስረት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነገር ነው ። አናርኪስቶች ዛሬ በግለሰብ ግድያ ላይ አተኩረው ታጋይ ጓዶቻችንን ቢገድሉ በነዚሁ ጓዶች ቆራጥ የርእዮተ ዓለም ትግል ጨርሰው ተጋልጠው ርቃናቸውን መቆማቸውን ማመናቸው ነው ።

ስለሆነም ተጋልጠው በሕዝብ ትግል የተተፉትን አድኃሪዎች በግልጥ መሣሪያ ይዘው በአብዮቱ ላይ እንዲያምጹ ያስገደዳቸው ተራማጆች በፖለቲካው ትግል ድልን በመቀዳጀታቸው ነው ። ይህንን ድል አናርኪስቶች በግለሰብ ግድያና በተራማጆች ሠፈር ሽብር ለመንዛት በመሞከር ሊያድበሰብሱትና እንዲያም ሲል ሊቀለብሱት ይሞክራሉ ።

ነገር ግን አብዮታውያን ለነቃ ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ ሕዝብ ትግል በሚል መፈክር ስር ተሠልፈው የሚታገሉት የተደራጀና የታጠቀ ፀረ ሕዝብ ትግልን በተደራጀና በታጠቀ ሕዝብ ትግል ለመቋቋም እጅግ አኩሪ መሆኑን ስለሚቀበሉት ነው ። ስለሆነም በንቃትና በድርጅት ትግላቸው የገፉ ታጋዮች የአድኃሪ ኃይሎችን ፀረ ሕዝብ አመፅ ለመቋቋም ታጥቀው ይነሳሉ እንጂ አናርኪስቶች እንደሚመኙት በዚህ ተደናግጠው ከነፃነቷ ትግል መድረክ አይወርዱም ።

የነጓድ ፍቅሬንና የተቀሩትን የትግል ጓዶቻችንን ንጹሕ ደም ለመበቀል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው መንገድ እነዚህ ጓዶች የሞቱለትን የነፃነት ተጋድሎ ወደፊት ይገፉታል ። አድኃሪዎች በተራማጆች ሠፈር ሽብር ለመንዛት ቢሞክሩ ተራማጆች ደግሞ ለአድኃሪዎች ሠፈር እጥፍ ድርብ ሽብር ይነዛሉ ። ታጋዮች በአድኃሪዎች መገደል የሌሎች ታጋዮችን ቁጣ ቀስቅሰው የቀልባሾችን ዕድሜ የዚያኑ ያህል ያሳጥሩታል እንጂ አድኃሪዎች በሚነዙት ሽብር አብዮት አይፈታም ።

የኢትዮጵያ ተራማጆች በሀቀኛና በመራራ የርእዮተ ዓለም ትግል የአናርኪስቶችን ተራማጅ ካባ ገፈው አጋልጠዋቸዋል ። እነጓድ ፍቅሬ መርዕድ በዚህ ትግል ውስጥ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ በሚገባ አበርክተው በትግሉ አፍላ ውስጥ እንዳሉ ወድቀዋል ። ግን የትግሉን አርማ ጨብጦ ወደፊት ለመጓዝ ሌሎች እጆች ተዘረጉ እንጂ የነጓድ ፍቅሬ የነፃነት ዓላማ አብሯቸው አልወደቀም ። እነጓድ ፍቅሬ የአብዮት ልጆች ናቸው ። አብዮት ምንጊዜም ቢሆን የትም ቢሆን ወደፊት ለመራመድ የገዛ ልጆቿን ትሰዋለች ። ጠላቶቿ አይጋፈጡላትም ። ጠላቶቿ ሊገድሏት ይፍጨረጨራሉ እንጂ አይሞቱላትም ። የሚጋፈጡላት የሚሞቱላት የገዛ ልጆቿ ናቸው ። አብዮት ልጆቿን ትበላለች የሚባለውም ለዚህ ነው ።

« አብዮታዊት ኢትዮጵያ » እነጓድ ፍቅሬን ለዘለዓለም ስታስታውሳቸው ትኖራለች ። እነዚህ ጓዶች ለአብዮቱ እስከመጨረሻ እንደታመኑት ሁሉ ተራማጅ ጓዶቻቸው በፈሰሰው ንጹሕ ደማቸው ፊት የትግል ቃል ኪዳናቸውን ያድሳሉ ። እንደነሱው እስከሞት ድረስ ለአብዮቱ ይሠራሉ ። እንደነሱ ይታገላሉ ። እንደነሱ ይሞታሉ ። አብዮቱ ግን ምን ጊዜም ወደፊት ይገፋል ። በታጋይ ጓዶች ማገዶነት የሚቀጣጠለውን የአብዮት ነበልባል ሊያጠፋው የሚቻል ምንም ዓይነት ኃይል የለምና ።

ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ።

